1. ተከሣሽ ከክሱ አስወጥቶ /Ex-parte/ ጉዳዩ መታየቱ የሚቀጥለው ተከሣሹ ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ችሎት ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ጉዳዩ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ መልሱን በጽሁፍ ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀረቡታል እንጂ በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለከልም፡፡



ሐምሌ 29 ቀን 1997

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አክስዮን ማህበር

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

## ፍ ር ድ

በዚህ መሠረት ለቀረበው ክርክር መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የጠቅላይ ፍ/ቤት የተቀበለው ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩ በሰበር መታየት ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ መልስ ሰጪም ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ ክርክሩን አቅርቦአል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሣሽ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠቱን አውቆ ለተሻሻለው ክስ መልስ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 73 መሠረት ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረጉ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የጣሰ አሠራር ነው በማለት በሰበር እንዲስተካከልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ክርክር የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆጠር ስላለበት ቀደም ብሎ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ ቢሆንም ለተሻሻለው ክስ መልስ የመስጠት መብቱ ሊቀርበት አይገባም የሚል ነው፡፡ መልስ ሰጪ በዚህ ጉዳይ ላይ መለሱን በጽሁፍ በማቅረብ የክሱ መሻሻል ቀደም ሲል የተሰጡትን ትእዛዞች የሚሽር ባለመሆኑ አመልካች ለተሻሻለው ክስ መልስ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ በሁለቱም ፍቤቶች ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት መኖሩን አያሳይም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካች መልስ ለማቅረብ በተቀጠረበት ቀን መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መታዘዙን

ተገንዝቧል፣ በተሻሻለው ክስ መልስ ሊያቀርብ አይገባም የሚል ትእዛዝ የተሰጠውም ቀደም ብሎ የተሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተረድቷል። በዚህም መሠት ጉዳዩን በአግባቡ ለማስተናገድ የአሁኑ አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ዕለት መለሱን ይዞ ባለመቅረቡ የሚከተለው ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለውንና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ነጥቦች መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል።

አንድ ተከሣሽ ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረበት ዕለት መልሱን ይዞ ካልቀረበ ክርክሩ በሌለበት የሚሰማ መሆኑ ፍርድ ቤቱ በሚልክለት መጥሪያ ላይ እንደሚገልጽለት በፍሥ.ሥ.ሕ.ቁ 233 ላይ ተደንግጓል። በሌላ በኩል የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቀ 70 ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ ተከሣሹ ያልቀረበው የተላከለት መጥሪያ ደርሶት ከሆነ ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንደሚቀጥል ይደነግጋል። እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ሁለት በተለያዩ ጊዜ የሚከናወኑ የሙግት ደረጃዎችን የሚመለከቱ ቢሆኑም የተከሣሽን መቅረት አስመልክቶ የሚያስከትሉት ውጤት ተመሳሳይ ይመስላል። የጽሁፍ መልሱን ሳያቀርብ የቀረ ተከሣሽ በ233 መሠረት በሌለበት ጉዳዩ እንደሚሰማ ጉዳዩ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ ተከሣሽም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ በቁጥር 70(ሀ) መሠረት ትእዛዝ የሚሰጥበት ይመስላል። የሁለቱም ድንጋጌዎች የአማርኛ ቅጂ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን መቅረትና ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን መቅረት አንድ አይነት ውጤት ያላቸው እንደሆነ የሚገልጹ ቢሆኑም የሁለቱም የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ግን የተለየ ጽንሰ ሃሳብ የሚያስተላልፉ ናቸው።

የእንግሊዝኛ የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ድንጋጌ ስለ Ex-part ሲናገር የ233 ግን የሚደነግገው ስለ default proceeding ነው።ሁለቱም የተለያየ ይዘት የተለያየ ውጤት ያላቸው ናቸው።

የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ቅጂ

> 70 where the plaintiff appears and defendant does not appear when the suit is called on for hearing (a) if it is proved that the summons was duly served, the suit shall be heard ex-parte

በማለት ሲደነግግ አግባብነት ያለው የ233 ክፈል ደግሞ

> …. The court shall cause… requiring him to appear with his statement of defense to be fixed in the summons and informing him that the case wile be proceeded withnotwithstanding that he does not appear or that he appears without his statement of defense. በማለት ይደገግጋል።



ሁለቱን የእንግሊዝኛ ቅጂዎች በማነጻጸር ለመገንዘብ እንደሚቻለው ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሽ መልሱን ይዞ ባይቀርብ የሚከተለው ውጤት ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባይገኝ ከሚከተለው ውጤት ጋር አንድ አይነት አይደለም። የ233 ድንጋጌ መለሱን ባያቀርብም የጉዳዩ መሰማት እንደሚቀጥል (default proceeding) ከሚይሳይ በቀር ተከሣሽ ከክርክር እንዲወጣ የሚያደርግበት ሥርዓት አለመኖሩን ያሳያል። በሌላ በኩል በ70(ሀ) ስር ያለው ድንጋጌ ጉዳዩ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን የቀረ ተከሣሽ ጉዳዩ እሱ በሌለበት መቀጠል(default proceeding) ብቻ ሳይሆን ከክርክሩ እንዲወጣ (ex-part) እንደሚደረግ በግልጽ ያስቀምጣል። ይህም በአማርኛ ቅጂ ላይ ያለው አገላለጽ በእንግሊዝኛው ላይ ያለውን ሃሳብ በትክክል አለማስተላለፉን ያመለክታል።

የትርጉም ልዩነት ሲኖር የአማርኛውን ቅጂ በመውሰድ ዕልባት መስጠት ይቻላል በማለት ጉዳዩ ማጠቃለል አንዱ አማራጭ ነው። ሆኖም ይህ አማራጭ አሁን በያዝነው ጉዳይ በግልጽ የሚታየውን የትርጉም ስህተት እንዲቀጥል የሚያደርግ በመሆኑ ትክክለኛ አማራጭ ነው አንልም። ይልቁም የተከሰተውን የትርጉም ልዩነት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማ እንዲሁም ተከሣሽ በቀረበበት ክስ የመደመጥ መብትን ይበልጥ ሊያስከብር በሚችል ሁኔታ መተርጐም በበለጠ የፍትህ አስተዳደርን ዓላማ በበለጠ ስለሚያሳካ የእንግሊዝኛው ቅጂ መከተሉን መርጠናል።

በዚህም መሠረት አንድ ተከሣሽ ከክስ እንዲወጣ መደረግ ያለበት ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እንጂ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ካልቀረበ መሆን የለበትም። ይህ አተረጓጐም ተከሣሹ መልስ ለመቀበል በተያዘ ቀጠሮ ሳይቀርብ ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል የሚል ጥያቄ ማስከተሉ የሚቀር አይደለም። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ፍርድ ቤት የሰጠው ቀጠሮ ሳይከበር ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል ከሚል ሌላ ጥያቄ ጋር ተያይዞ መመለስ ያለበት ነው።

በሙግት ሂደት ፍርድ ቤት የተለያዩ ጉዳዮች መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቀጠሮዎችን ይሰጣል ሆኖም ፍ/ቤቱ የሰጠው ቀጠሮ በአንዱ ወይም በሌላው ተሟጋች በተሰተጓጎለ ቁጥር ለመስተጓጎሉ ምክንያት የሆነው ወገን ከክርክ እንዲወጣ (Ex-parte) አይደረግም። የቀጠሮው አለመከበር ቀጠሮ ከተሰጠሰት ምክንያት ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ በየጉዳዩ የተለያየ ትዕዛዝ የሚሰ ቢሆንም መሠረታዊው የጉዳዩ ሂደት የሚስተናገደው በሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 7 በሚገኙት መርሆዎችና ድንጋጌዎች መሠረት መሆን አለበት። በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 194 እንደተገለፀው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው የገልጻል። በዚህም መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ መልሱን ከማቅረብ ጋር ተያየዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀሩበታል። በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለክልም።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አሁን አመልካች በተሻሻለው ክስ ላይ መልስ መስጠት አትችልም የተባለው ቀደም ብሎ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን መለሱን ይዞ አለመቅረቡን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሹ መልሱን ሳያቀርብ ቢቀር የጽሁፍ መልስና የማስረጃ ዝርዝር የማቅረብ ዕድሉን ከሚያጣ በቀር ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን መታዘዝ አልነበረበትም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ተከሣሽ ሕጉ ከሚፈቅደው ሁኔታ ውጪ ከክርክር ውጪ ማድረግ በጉዳዩ ላይ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ ክሱ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሲሰጥ ተከሣሽ መልስ ማቅረብ አትችልም የተባለው ከዚህ ሥነ ሥርዓት ግድፈት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው፡፡ አመልካቹ ከክርክሩ መውጣት ሳይኖርበት አውጥቶ ለተሻሻለው ክስ መለስ አታቀርብም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን በማመን ይህን ግድፈት ማስተካከል ሲገባው አልፎታል፡፡ በመሆኑም የሰበር ችሎት የተፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ግድፈት በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 211 ስር በተደነገገው መሠረት ማሰተካከል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ውሣኔ

1. የአሁን አመልካች በከፈተኛ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ከክርክር ውጪ የተደረገው በአግባሱ ስላልሆነ ወደ ክርክሩ ይግባ፡፡
2. ለተሻሻለው ክስ መልስ ማቅረብ እንዲችል በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻሻለው ክስ ግልባጭ ይሰጠው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡



## ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15992

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

መልስ ሰጪ፡- ወ/ት ሶስና አስፋው

*ውል- ስለውል አፃፃፍ/ ፎርም/- ስለ ውል አፃፃፍ ነፃነት- ስለ ውል አጻጻፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈጸም የሚያስከትለው ውጤት - የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች፣- የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች በስምምነት ስለሚሆን ያጻጻፍ አይነት - የግዴታዎች ቀሪ መሆን - ስለ ይርጋ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1719፣1720/1/ 1723፣ 1726 ፣1727፣ 1845*

በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተደረገው የኪራይ ውል በሁለት ምክንያት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1726/1/ እና 1727/1/ መሠረት የውል ረቂቅ እንጅ አስገደጅነት የለውም፣ አመልካች ከጠየቀው ኪራይ ውስጥ እስከ 8/2/89 ያለው መጠየቅ ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት አመት ያለፈው በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፣